# ችጋ ትዝታዬ

የት ጠፋህ፣ የት ተደበቅህ ችጋ፣

ማግኘት ተሳነኝ በአሳር በፍለጋ፣

አንተን ስተዉህ ታጥረህ ነበር
በአጋምበቀጋ፣

ዱር አራዊቶችምአነር፣ ነብር፣
ቀበሮ፣ ጅብ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣
ድኩላ፣ ሚዳቋ፣ ቆቅ ጅግራ ዘብ
ቋመዉልህ እንደነበር አይዘንጋ፣

እነሱ ከዱህ፡ ወይስ ከዳሀቸዉ
እዉነቱን አጫዉተኝ ኩራቴ፡ የእኔ
ሸጋ፣

ስትቧርቅ፣ አትንኩኝ ባይነትህን
ስታሳይ በክረምት፣ ለስለስ ስትልም
በበጋ፣

አጼ ምንጭምእያደሰችህ፣
እያደረገችህምለግላጋ፣

ለሁሉምመመኪያ ነበርክ እንዴት
በቀላሉ ተጋለጥክ ለአደጋ፣

የአንተ ዉለታህ እኮ ብዙ ነዉ
አያልቅምቢነገር፣ ቢወጋ፣

ከመታዘል፣ ቅል ማሰር፣ ቅል ከማሰር
ቅል መፍታት፣ ቅል ከመፍታት
በዉቅያኖስ ማንሳፈፍ ያለ አለንጋ፣

በጉራ ራሴን እያልኩየችጋ ጌታ፣
የዓባይ ገፈታ ትናፍቀኝ ነበር
ከምሽት እስከሚነ ጋ፣

ከትምህርት ሆነ ከሥራ ሞጣለዕረፍት
ስመጣ አልመለስምነበር ሳልደርስ
አንተ ጋ፣

ገና ከሩቅ ሳይህ ነበር ልብሴን
የምታስጥለኝ እንደ እብድ፣
ጭንቅላቱ እንደተናጋ፣

አንተ ዉስጥ ለመግባትና ለመንጣለል
የማደረግዉ ጥድፊያ እዉነትም
የተረበሸ ሰዉ፡ ያልተረጋጋ፣

አብደህ የምታሳብድ፣ አንዱ ሌላዉን
በማጥለምኩታራዉ ሁሉ ሲዋጋ፣

ተዉበማለት ፈንታ አድልዎ አድርገህ
ጎበዙ በላይህ ላይ እጁን ሲዘረጋ፣

ደካማዉግን ወርዶ ለትህን ለመንካት
አካሉንና መንፈሱን ሲያናጋ፣

ጥልቅ እኮ ነበርክ፣ ዝልል፡ በሰማይ
እግር እጥፍ፡ በእጅ ሸበብ አድርገን
ስንዶልብህ ድበርክን የማታስነካ፣
የምትበልጥ ከጨሞጋ፣

ይግረማችሁ ብለህ ዳባ ማጠቢያን፣
መክሊትን፣ ደወልን፣ ዘንዶ ዉኃን
አብረህ ለጥፋት ስታንጋጋ፣

ሰዉን ብቻ ሳይሆን የሞጣ፣ የበሩ፣
የኮሊሳ ጊዮርጊስ፣ የላይ፣ ታችና
ወብ ማርያም፣ መክሊት ሚካኤል ታቦቶ
እጎዳለሁ ብለህ ሳትሰጋ፣

ማነ ዉልብየሰጠህ፣ ሚኒሸር፣
አልቢን፣ ዳንዴ ያስተጠቀህ፣ አየር

ለዉጥ የሚሉት ነው ወይስ እሱ
እንዲነግስ ያደረገዉ መንጋ፣

ሽፍትነቱ ይብቃ፣ እኮ ወደ
ነበርክበት ተመለስ ችጋ።

ልጆችህ ተነስተዋል ሊያላቅቁህ
ከተያዝክበት የድርቀት መንጋጋ።

By Gashe Mersie Ejigu